November 1, 2005

# አስቸኳይ ጠንካራ የትግል ጥሪ
# ለኢትዮጵያውያንና ለወዳጆቿ ሁሉ !

በኢትዮጵያ የወያኔ/ኢህአዲግ አምባገነንና አረመኔ መንግሥት ለአሥራ አራት ዓመት ያደረሰብን ግፍና በደል አልበቃ ብሎት እነሆ ዛሬም የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት መሪዎች በመዲናችን በአዲስ አበባ ስብሰባ በሚያደርጉበት ወቅት በአደባባይ ሰላማዊ ዜጎችን በመረሸን፥ በመጨፍጨፍ፥ በማሰርና በማፈን ላይ ይገኛል።

ስለዚህ 1ኛ/ ወያኔ/ኢህአዲግ እየፈፀመ ያለውን አሰቃቂ የአደባባይ ርሸና፣ የግፍ ግድያና አፈና የማሰር ተግባሩንም በአስቸኳ እንዲያቆም የዓለም ሕብረተሰብ በተለይም የአሜሪካና የእንግሊዝ መሪዎች አስቸኳይ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) አጥብቆ ያስታውቃል።

2ኛ/ ይህ ፋሽስታዊ ድርጊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መምጣቱን የዓለም መንግሥታት ኤምባሲዎችን ማሳወቁ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የማንኛችንም በውጭ የምንገኝ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ኃላፊነት እንዳለብን በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ለሁሉም እናቀርባለን።

3ኛ/ ማንኛውም የዓለም ሕብረተሰብ አባል ከአምባገነኑ ወያኔ/ኢህአዲግ መንግሥት ጋር ያለውን ወዳጅነት እንዲያቆም በጥብቅ እናሳስባለን።

4ኛ/ የአምባገነኑና አረመኔው ወያኔ/ኢህአዲግ መንግሥት መሪ በሰላማዊ ትግል የማያምን ለመሆኑ በተግባር በአደባባይ በቀን በጭፍጨፋ፣ በአፈናና በእስራት ያሳየ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከሰላማዊ ትግሉ ጐን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) ከሚያደርገው <u>የሁለገብ ትግል</u> የተጣመረ እንዲሆን ትብብራችሁን እጅግ አጥብቀን እንጠይቃለን።

5ኛ/ የተወሰኑ ኃያላን አገሮችና ዜጎቻቸው እውን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን እንደማይመኙልን ታሪክ ታላቁ ምስክራችን ስለሆነ የአባቶቻችንን ጀግንነት ደግመን በማሳየት ከባንዳው ወያኔ መንጋጋ ኢትዮጵያን አላቀን ክብሯን ለማስመለስ ቆርጠን እንነሳ።

የወያኔ እብሪተኛ መንግሥት በለላማዊ ትግል ብቻ እንደማይወገድ ተረድተናል። ሁለገብ ስንልም በምናገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉን አቀፍ ትግል ማካሄድ ማለት ነው። <u>ወቅቱም ይፈቅድልናል</u>። ለሰላማዊው ትግሉም አጋር ነው ብሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር እርምጃውን ቀጥሏል።

በትግላችን ብርታትን የሚሰጠን ፈጣሪ አምላካችን ይረዳናል !
በቆራጥ ልጆቿ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ከጫንቃችን ይወርዳል!

***<u>ቆራጥ ልጆቿ ተነሱ ኢትዮጵያን እናስከብር</u> !***

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር።

**ETHIOPIAN NATIONAL UNITED FRONT (ENUF)**
**P.O. Box 2206 Washington D.C. 20013 U.S.A.**
**Tel. (214) 594-2102 Fax (909) 985-7741**
**www.enufforethiopia.org**